የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 እና 10

1. አይሁድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ምን እንዲደረግ ተስማምተው ነበር?
ሀ)እንዲገደል
ለ)ከምኩራብ እንዲወጣ
ሐ)ከሀገሩ እንዲሰደድ
መ)ሁሉም

2. ምንደኛ ማለት ምን ማለት ነው?
ሀ)የተቀጠረ ሠራተኛ ለ)ንጉሥ ሐ)ባሪያ መ)ሁሉም

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ በጎች ያለው ማንን ነው?
ሀ)ጻድቃን ለ)እፅዋትን ሐ)እንስሳትን መ)ሁሉም

4. አይሁድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በድጋሜ ድንጋይ ለምን አነሱ?
ሀ)ስለመልካም ሥራው
ለ)ነብያትን አያከብርም ብለው
ሐ)ሰንበትን ሽሯል ብለው
መ) እራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሏል ብለው

5. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10:34 "እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ" የሚለውን ቃል በኦሪት መጽሐፍት በየትኛው ይገኛል?
ሀ)ትንቢተ ኢሳይያስ 7:14
ለ)ትንቢተ ሚክያስ 1:5
ሐ)መዝሙር 81:6
መ)መልስ አልተሰጠም

6. በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሰዎች በየት ሳለ ነው ያመኑበት?
ሀ)በምኩራብ ለ)በቤተመቅደስ ሐ)በናዝሬት መ)በዮርዳኖስ

7. በመቅደስ መታደስ በዓል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በየት ነበር?
ሀ)በሰሎሞን መመላለሻ ይመላለስ ነበር
ለ)በስውር ከአይሁድ መካከል
ሐ)በዮርዳኖስ
መ)መልስ አልተሰጥም

8. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ዕውር ሆኖ የተወለደው በማን ጎጢአት ነው አለ?
ሀ)በራሱ ጎጢአት
ለ)በወላጆቹ ጎጢአት
ሐ)የእግዚአብሔር ሥራ እንዲገለጥ እንጂ በማንም ጎጢአት አይደለም
መ)ሁሉም

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው እንዴት አዳነው?
ሀ)ምራቅ እንትፍ ብሎ ጭቃ ለውሶ ዐይኑ ቀብቶ በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ ብሎ
ለ)ዳስሶት
ሐ)ተከፈት ብሎ
መ)ኤፍታህ ብሎ

10. ሰሊሆም የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?
ሀ)የተቀባ ለ) ምልክት ሐ)የተላከ መ)ሁሉም

11. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ላይ "በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ " ሲል ምን ማለት ነው?
ሀ)በተአምራት አምላክነቱን ለዓለም መግለጡን ሲያሳይ
ለ)በሕይወተ ሥጋ ሳለ በተአምራቱና በትምህርቱ ለሰው ልጆች ብርሃን መስጠቱን መናገሩ ነው
ሐ)በተአምራቱ የዕውራንን ዓይን እንዳበራ ሲናገር
መ)ሁሉም

12. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ላይ የዕውሩ ሰው ወላጆች "ሙሉ ሰው ነው እርሱ ስለ ራሱ ይናገራል " ያሉት ለምንድነው?
ሀ) የክርስቶስን ተአምር ለመመስከር
ለ) ክርስቶስ ዓይኑን እንደከፈተ ለመመስከር ስለፈሩ
ሐ) ልጃቸው ሲናገር እነርሱ ከአይሁድ ሮጠው ሊሸሹ ስለፈለጉ
መ) ሀ እና ሐ

13. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9 ላይ ጌታ የፈወሰውን ዕውር አይሁድ በመጨረሻ ምን አደረጉት?
ሀ)በእርሱ ምክንያት ሁሉም ጌታን አምነው ተቀበሉ
ለ)ጌታን እንዲክድ አሳመኑት
ሐ)ከምኩራባቸው አወጡት
መ)ሸሽገው ወደ ሌላ አውራጃ አሸሹት

14. የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ምን በመባል ይታወቃል?
ሀ)አንቀጸ ጻድቃን ለ)አንቀጸ ብጹዓን ሐ)አንቀጸ አባግዕ መ)አንቀጸ ክብር

15. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ላይ በረት የምን ምሳሌ ነው?
ሀ)የቤተክርስቲያን ለ)የዓለም ሐ)የመንግሥተ ሰማያት መ)ሀ እና ሐ

16.በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ላይ በር የተባለው ምንድነው?
ሀ)የቤተክርስቲያን የግቢ በር
ለ)ወንጌል
ሐ)የከተማ በር
መ)የምእመናን ቤት መግቢያ

17."በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው" ሲባል በር የተባለ ምንድነው?
ሀ)ነቢያት የተናገሩት ትንቢት
ለ)ነቢያት የቆጠሩት ሱባዔ
ሐ)የግሪክ ፍልስፍና
መ)ሀ እና ለ

18."ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው " የተባሉት ሰዎች ውስጥ የሚካተቱት እነማን ናቸው?
ሀ)ቴዎዳስ ለ)የገሊላው ይሁዳ ሐ)ስምዖን ቀነናዊ መ)ሀ እና ለ

19."በእኔ በኩል የሚገባ ይድናል፣ ይገባልም ይወጣልም " የሚለው ላይ ይወጣል የተባለው ምን ለማለት ነው?
ሀ)ከሃይማኖት ወጥቶ በክህደት ይኖራል
ለ)ወንጌልን ለመስበክ ከቤቱ፣ ከሀገሩ ይወጣል
ሐ)በጌታ ስም ለመሰደድ፣ መከራ ለመቀበል፣ ለመሞት ይወጣል
መ)ለ እና ሐ

20. ቸር ጠባቂ ...
ሀ)ነፍሱን ስለ በጎቹ ይሰጣል
ለ)ተኩላ ሲመጣ የራሱ ሕይወት ለማዳን በጎቹን ጥሎ ይሮጣል
ሐ)በጎቹን አያሰማራም
መ)በጎቹን ከበረታቸው ብቻ ሆኖ ይጠብቃል